

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከሜይ 21-31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

## ከጁን 1-10፣ 11-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁን 2026

አዲስ አበባ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

በሜይ የሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች፣ በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶቸች ላይ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና ሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠሩት ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛ እና የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ባህር ዳር 21.9፣ ደብረ ማርቆስ 29.8፣ 25.4፣ ቢሾፍቱ 28.4፣ ጎሬ 34.3፣ 35.7፣ 28.8፣ ጅማ 36.5፣ 21.9፣ መተሃራ 27.6፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 37፣ 21.8፣ አዴት 30፣ አይራ 26.5፣ 20.2፣ ሐሮማያ 21.2፣ አለም ከተማ 22.4፣ አማን 27.6፣ 43.2፣ አምቦ 30.3፣ አርጆ 34.6፣ 24.4፣ 20.8፣ አይከል 35.9፣ በደሌ 25.3፣ 58.8፣ 25፣ ቦሬ 28፣ ቡሂ 21.6፣ ቡለን 51.4፣ ቻግኒ 20.2፣ 20.7፣ ጨዋቃ 32፣ ዳንግላ 34፣ 27.5፣ ደባርቅ 36.2፣ ደብርታቦር 36.8፣ ደብረ ወርቅ 21.8፣ ኢጃጂ 24.2፣ እነዋሪ 27፣ ፉኙዶ 20.6፣ 68.8፣ ጋምቤላ 21.7፣ 27.2፣ ጋቲራ 21.1፣ ገለምሶ 52፣ 24.3፣ 21.2፣ ወሊሶ 27.2፣ ጊዳአያና 27.3፣ 24.3፣ ጅግጅጋ 20.8፣ ሊሙገነት 35.3፣ ማንኩሽ 31.6፣ 24.6፣ መተማ 23.3፣ ሞጣ 26.6፣ 28፣ አዳማ 22.1፣ ኑራ ኤራ 22.21፣ ሰኮሩ 30.7፣ ሻሁራ 24፣ ሻምቡ 33.5፣ ቴፒ 21.3፣ 36፣ 30.2፣ ተርጫ 34.8፣ ወራቤ 25.7፣ 29.9፣ 24.2፣ ወላይታ ሶዶ 27፣ ዩትኖራ 24.3፣ 27.4፣ ባቱ 29.2፣ አቦሞሪንጋ 26፣ አንጋጫ 22፣ አሺ 32፣ 24፣ 34.8፣ 24፣ ቡልቂ 26.1፣ 26.5፣ ጉበይሬ 25.5፣ ጉቢቲ 26.1፣ 30.4፣ 26.1፣ ሓደዋ 21.5፣ ሃራ 20.6፣ ኦንጋ 54.3፣ 38.5፣ ሼንዲ 36.5፣መንድር 13 30.4፣ 32.2፣ 26.4፣ መንደር 11 33.5፣ 28.5፣ እንዲሁም ዉልበረግ 29.3፣ 24.2፣ ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በሃያ ዘጠኝ (29) የአገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute





ምስል1: ከሜይ 21 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮጉድሩ ወለጋ፣ ቄሌም ወለጋ፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖቸ፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን ዞኖቸ፣ ከአማር ክልል ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሃላባ፣ ሃዲያና ከንባታ ዞኖች ላይ ከ16-147 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ሁሩጉድሩ ወለጋ፣ ቄሌም ወለጋ፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖቸ፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን ዞኖቸ፣ ከአማር ክልል ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ስልጤ፣ ጉራጌ፣


ሃላባ፣ ሃዲያና ከንባታ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31 /2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31 /2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31 /2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የሜይ የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛዉ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከእርጥበታማ እስከ በጣም እርጥበታማ ሁኔታዎች እንደነበሩ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ እንደ ቦቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እድገት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፣ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ ዝናብ ምንም እንኳን በጥቂት ቦታዎች ላይ አሉታዊ ጎን ቢኖረውም ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ ጠቀሜታው የጎላ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በብዙ የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት አስቀድመው የማሳ ዝግጅት እንዲያከናውኑና በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበርዉ (ካርታ 4)።

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በሜይ የሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ኦጋዴን፣ በላይኛውና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ በመካከለኛውና ታችኛው ተከዜ እንዲሁም በላይኛውና በመካከለኛ ገናሌ ዳዋ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛው አባይና ታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለገፀ ምድርም ሆነ ለከርሰ ምድር የውሃ ሀብት መሻሻል አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው። በአንጻሩ ግን በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ መረብ ጋሽ፣ አይሻ፣ በመካከለኛና ታችኛው ገናሌ ዳዋና ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም ታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተው ነበር (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፣ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል:: በጁን በመደበኛው ሁኔታ የተስፋፋ የዝናብ መጠንና ስርጭት የተሻለ መልክ የሚኖረው ከወሩ ከመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ጀምሮ ነው። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-24 ቀናት ያህል ይዘንባል። ይሁንና በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ30-100ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ3-16 ቀናት ያህል ይዘንባል። ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁን የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

### 2.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁን የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡፡


Ethiopian Meteorology Institute

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች እና የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በመካከለኛወ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡


## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በጁን የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአፋር ክልል፣ በሰሜንና በደቡም ምዕራብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሊይ ከ32 እስከ 40 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10 /2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁን 1-10 /2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

| | | |
|---|---|---|
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች የደቡብ ጎንደር እና የባህርዳር ዙሪያ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን፣ ሲቲ፣ ኤረር፣ ጃራር፣ ዶሎ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 2.2 እ.ኤ.አ ከጁን 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁን ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ሳምንት ነው፡፡

በመጪዎቹ የጁን ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄድ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ ፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የመኸር እርሻ ስራ ቀድመው የሚጀምሩና የበልግ ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ እና የደቡብ ኦሞ ዞኖች | ➢ የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>➢ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት | ➢ የእርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቅየት እና የውኃ መተኛት<br>➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ የአረም መከሰት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት፤<br>➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር | ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የአፈርና የውሃ እቀባ ስራዎችን መስራት፤<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ የአየር ጠባይ መረጃዎችን መከታተልና ተግባራዊ ማድረግ፤ |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን ፣ የመካከለኛዉና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ፋፈን፣ ሲቲ፣ ኤረር፣ ጃራር፣ ዶሎ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | ➢ ለመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ምቹነት<br>➢ ፍሬ በማፍራትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ ለከተማ አካባቢ ግብርና ስራ | ➢ ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት መኖር፤<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤<br>➢ የአፈርና ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆን | ➢ የመኸር ሰብሎችን ጊዜውን ጠብቆ መዝራት<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ የአፈር እቀባ ስራ ማከናወን፤<br>➢ የእንስሳት ግጦሽ ሣር በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

Ethiopian Meteorology Institute

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከባድ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| መካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ ላይኛው እና መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ ላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አዋሽ፣ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ የውሃ ይዘት መጨመር<br>• ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>• የኩሬና የወንዝ የውሃ መጠን መጨመር | • የከተሞች የዉሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት<br>• ወንዝ በደራሽ ውሃ ሙላት | • የጎርፍ ቅድመ መከላከል ስራዎች መስራት<br>• የዝናብ ውሃን ማሰባሰብ እና ማከማቸት<br>• የውሃ መውረጃ ቱቦዎች ማጽዳት |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በላይኛው ባይ፣ኦጋዴን፣ በመካከለኛው አዋሽ፣ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም ኦሞ ጊቤ | • መጠነኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት መሻሻል | • አንጻራዊ የትነት መጨመር<br>• የደረቅ ሰሞናት በመብዛት | • የዉሃ ብክለት መቀነስ<br>• የሚገኘውን መጠነኛ ዉሃ በአግባቡ መያዝ<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በመጠቀም የጊዜ ተመን እቅድ ማዘጋጀት |
| **በደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ መረብ ጋሽ፣ አይሻ ኦጋዴን፣ መካከለኛውና በታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • ዉሃን በአግባቡ መጠቀም<br>• የውሃ መቆጠብያ ዘዴዎችን መተግበር<br>• የውኃ ማከማቻ (water harvesting) መርህ ግብሮች ማጠናከር |